የሰ/መ/ቁ. 58540

ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል - ጠበቃ ቶማስ ገ/አብ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- ሲስተር ገነት ወንድሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት ያደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የመሠረቱት የስራ ቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የስራ ቅጥር ውሉ የተቋረጠው የአመልካች እናት ድርጅት በመክሰሩ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብሎ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ካናዳ የሚገኘው የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት ስለመክሰሩ የአመልካች ድርጅት በማስረጃዎች አረጋግጠዋል፣ የተጠሪ ምስክሮች ቃል ግን ይህንኑ የአመልካች ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር የሚያስተባብል አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የስራ ስንብት ክፍያና የ29 ቀናት የዓመት ፈቃድ ክፍያ ብቻ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የስራ ስንብቱ ከሕግ ውጪ የተከናወነ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ክፍያ አይነት በተጨማሪ የካሣ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተባለው በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ መሰናበት የነበረባቸው በቅነሣ መልክ መሆን ይገባው ነበር ተብሎ የስራ ስንብቱ ከሕገ ውጪ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ

ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ ባቀረቡት ክርክር በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የሻረው የአመልካች ድርጅት ጠቅላላ ስራ መዘጋቱ በበቂ ማስረጃ አልተረጋገጠም፣ ስራው እየቀዘቀዘ ነው እንዳይባል ደግሞ በቅነሣ መልክ ስንብቱን አላከናወነም በማለት መሆኑን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው አመልካች ድርጅት ማዕከል ውስጥ በወቅቱ አንድ ህፃን ብቻ መቅረቱ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት በመከሰር ላይ ያለ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በሚገባ ማረጋገጡን የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በተገቢው መንገድ ሣይረጋገጥ የተያዘ ድምዳሜ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በደፈናው በተገቢው ሣይረጋገጥ ነው በሚል ከመሆኑ ውጪ ተገቢ ያልሆነበትን፣ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች የሰጡት ቃል ተቀባይነት የማይኖርበትን  ህጋዊ ምክንያት ሣይጠቅስ ነው፡፡ የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ስለመሆኑ ስለ ፍርድ አሰጣጥ የሚደነግጉት ከቁጥር 341 ጀምረው ያሉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ያለሕጋዊ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር አይገባም፡፡ በመሠረቱ የበላይ ፍርድ ቤት በበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችንም የማይቀበልበትን ምክንያት በግልጽ ጽፎ ውድቅ ማድረግ እንጂ በደፈናው በተገቢው አልተረጋገጡም በማለት ሊያልፈው አይገባም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሰበትን ድምዳሜ ያልተቀበለበት አግባብ የዳኝነት አካሄዱን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም ከተባለ ደግሞ የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተቀጠሩበት ስራ መቀዝቀዙን በሚገባ ያረጋገጠ ሲሆን አንድ አሰሪ ስራው በመቀዝቀዙ ምክንያት ሰራተኛውን ሊያሰናብተው የሚችልበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ተዘርግቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይም የተጠሪ ስንብት በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ መሠረት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካች ተጠሪን በቅነሣ ሥርዓት ያሰናበታቸው መሆኑን አላስረዳም በማለት የያዘው ምክንያት የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነገር ተጠሪ ጋር በተመሣሣይ ሁኔታ ተቀጥረው ስራ በመስራት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ስራውን እየሰሩ ስለመሆኑ የተረጋገጠበት ሁኔታ የለምና፡፡ በአጠቃላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሻረው በሕጉ አግባብ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የመሠረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87901 ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58407 ታህሣሥ 07 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ